# ወያኔ/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ለም መሬት ለሱዳን ለማስረከብ ቅድመ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ነው ፤

## ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
## የተሰጠ መግለጫ

**ጥር 14 ቀን 2001 ዓ. ም. ( January 22, 2009 )**

**ወያኔ/ኢሕአዴግ በሰሜን ምዕራብ ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከ1600 ኪሎ ሜትር በላይ እርዝመት እና ከ30-60 ኪ/ሜትር የጎን ስፋት ያለውን ውሃ-ገብ ለም መሬት ለሱዳን ለመቸርቸር ያደርግ የነበረውን ከፍተኛ ሥውር ደባ ከነሐሴ 1999 ዓ.ም. ( August 2007 ) ጀምሮ በተጨባጭ ማስረጃዎቸ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴው ሲያጋልጥ መቆየቱ የሚታወስ ነው።**

**በቀረቡት ተጨባጭ ማስረጃዎች ጥንካሬ ምክንያትም የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፓለቲካ ድርጅቶች ፣ የሃይማኖትና ሰብዓዊ ተቋማት ቁጣ የተሞላበት ተቃውሞአቸውን ማሰማታቸው የሚታወስ ነው። ከዚህም አልፎ በራሱ በወያኔ ፓርላማ ውስጥ ካሉ አባላት መካከል ጥቂት አባላት የሃገራቸው ዕድል በልጦባቸው ተቃውሞ በማሰማታቸው የሰብዓዊ መብት ገፈፋና መንገላታት እንደደረሰባቸው የሚታወቅ ነው።**

**ተሰጠ በተባለው መሬት የሚኖረው የአካባቢው ሕዝብም ከፍተኛ መፈናቀል ፣ ግድያና የሃብት መቃጠል ከደረሰበት በኋላ በቁጣ ተነሣስቶ ክረምቱን ተንተርሶ በወሰዳቸው ቆራጥ የሃገር ድንበር የማስከበር እርምጃዎች የሱዳን ጦር የኢትዮጵያን መሬት ለቆ እንዲወጣና ወደ ሃገሩ ተሻግሮ እንዲከርም አድርጎት ነበር።**

**አሁን ግን ክረምቱ አልፎ የአካባቢው መሬት ለእግረኛ ጦር አመች ስለሆነና የኢትዮጵያም ሕዝብ የተዘናጋ ስለመሰለው ፤ ወያኔ መሬቱን ለማስረከብ ከፍተኛ ቅድመ ዝግጅቶች በማድረግ ለይ መሆኑን የሚከተሉት ሁኔታዎች ይጠቁማሉ ፥**

**1ኛ/ ወያኔ/ኢሕአዴግ በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ካድሬዎቹን በድንበሩ አካባቢ ባሉ መንደሮችና የእርሻ ጣቢያዎች በማሰማራት የአካባቢው ሕዝብ "ስምምነቱ ትክክል ነው" በሚል ወረቀት ላይ እንዲፈርም እያንዳንዱን ግለሰብ በማስገደድ ላይ ይገኛል። ይህም ጉዳዩን ለፓርላማ አቅርቦ በማጸደቅ ስምምነቱን ሕጋዊነት ለማሰጠት የሚደረግ ዝግጅት ይመስላል።**

**2ኛ/ የወያኔ/ኢሕአዴግ ካድሬዎች ሕዝቡን በግዴታ ለማስፈረም ከሚያደርጉት ዘመቻ በተጨማሪ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ገበሬ ለሱዳን በተሰጠው ውሃ-ገብ መሬት በሚቀጥለው የአዝመራ ዘመን እንዳያርስ ፣ ከብቶቹን እንዳያሰማራና በሸንፋ እና በጓንግ ወንዞች ውሃ እንዳያጠጣ በጽሑፍና በቃል በከፍተኛ ደረጃ በማስጠንቀቅ ላይ ይገኛሉ።**

**3ኛ/ በጥር (January) 18, 2009 Afrique en ligne (Africa Online) የተባለው በዋናነት በፈረንሳይ ቋንቋ የሚታተም ድረ-ገጽ ጋዜጣ ኢትዮጵያን ሔራልድ ( Ethiopian Herald ) የተባለውን በእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚታተም ዕለታዊ የመንግሥት ጋዜጣ በመጥቀስ በቀጥታ የሚከተለውን አስፍሯል ፥**

> **" በሁለቱ ሃገሮች መካከል አልፎው አልፎው የሚነሱ አንዳንድ አለመግባባት የሁለቱን ሃገሮች የረጅም ዘመን ወዳጅነት አላሻከረውም ፤ በሱዳንና በኢትዮጵያ ድንበሮች የሚነሱ ችግሮችና በድንበሩ አካባቢ የሚከሰቱ ጦርነቶችም የውሃና ከብት ማገጃ ቦታ ፈላጊ ዘላኖች የሚፈጥሩት ችግር ነው ፤ አሁን ግን ስምምነት ላይ ተደርሷል።"**

**ከዚያም Ethiopian Herald ቃል በቃል የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊን በመጥቀስ ያቀረበውን እንደሚከተለው አስቀምጦታል ፥**

**" ስምምነት ደርሰናል ስንል የሱዳን ሕዝብ እርሻውን እንዲያርስ <u>ጉዌን በከለለው መሥመር</u> መሠረት መስማማታችንን ነው።"(ሰረዝ የተጨመረ)**

**አቶ መለስ "ስምምነት ደርሰናል" ሲል ሕዝብ በመጨፍጨፍ ፣ ምርጫ በመስረቅና የሃገርን ካዝና በማራቆት የታወቀውን እራሱ የሚመራው ፀረ-ኢትዮጵያና ሃገር ከሃዲው የወያኔ ቡድንን ነው። " ጉዌን በከለለው መሥመር " ሲል ደግሞ አፄ ቴዎድሮስ ተወልደው ያደጉበትንና በጉልምስናና በንጉሣዊ ዘመናቸው ኢትዮጵያዊነቱን አስከብረውለት የኖረውን መሬት ፤ አፄ ዮሐንስ አንገታቸውን የሰውለትንና በአጥንታቸው ያጠሩትን የድንበር ቦታ የሚጨምርና እንግሊዞች ሱዳንን በቅኝ ግዛትነት በሚገዙበት ወቅት ለጥጥ ማብቀያ የሚሆን ውሃ-ገብ መሬት ከኢትዮጵያ ቆርሰው ለመውሰድ ያደረጉት የድንበር መስመር ከለላ ሴራ ነው። ይህን የእንግሊዝ ሴራ ደግሞ የአፄ ምኒልክ እና የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥታት ውድቅ ከማድረጋቸውም በላይ ፤ የደርግ መንግሥትም አንጋፋ ኢትዮጵያውያን ምሁራንን በማሰባሰብ ድንበሩን በተመለከተ ባካሄደው ሰፊ ታሪካዊ ጥናት ለአንዴና ለመጨረሻ ሞቶ የተቀበረ ነው ብሎ ፋይሉን የዘጋበት ጉዳይ ነው።**

**አቶ መለስ ልክ በኤርትራ ድንበር ከለላ ጉዳይ እንዳደረገው ሁሉ ፤ ሱዳንን በተመለከተ ደግሞ የሞተና የበሰበሰ ውል ከመዝገብ ቤት አውጥቶ ኢትዮጵያን የሚጎዳበት መንገድ አገኝ ብሎ ከሱዳን ጋር በመነጋገር ላይ ነው። በእውነት እንነጋገር ከተባለና የድንበር ከለላ ጉዳይ ከተነሳ ፤ ኢትዮጵያ ሰፋ ያለ መሬት አሁን ሱዳን ተብሎ በሚጠራው ሃገር ውስጥ እንደተወሰደባት ታሪካዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ሆኖም ግን በኢትዮጵያ የስልጣን ቁንጮ ላይ 18 ዓመት የተቀመጠው የወያኔ ገዢ ቡድን ዓበይት ተልዕኮ አድርጎ የያዘው ሃገርን መቆራረስና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት ስለሆነ ፤ ሃገርን ከዚህ ፀረ-ኢትዮጵያ ቡድን ለማዳን ኃላፊነቱ በእያንዳንዱ ሃገር-ወዳድ ኢትዮጵያዊ ጀርባ ላይ ወድቋል።**

**ስለዚህ ይህን የድንብር ጉዳይ በEthiopian Herald መውጣቱና ብሎም በዓለም አቀፋዊ ጋዜጣ እንዲወጣ መደረጉ ፤ የክህደት ስምምነቱ ዓለም አቀፋዊ እውቅና እንዲያገኝ ወያኔ ከሚያደርገው የሴራ እርምጃ አንዱ ነው።**

**ውድ ወገኖቻችን ሆይ!**

**የሃገራቸው ዳር ድንበር ለም መሬት ተቆርሶ መሰጠቱን የተቆጩ በድንበሩ አካባቢ ያሉ ወገኖቻችን የሃገራቸውን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት ለማስከበር በአንድ በኩል ወያኔን በሌላ በኩል ሱዳንን እየታገሉ ባሉበት ወቅት አቤቱታቸውን ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ሕብረተሰብ እንድናሰማላቸው የእያንዳንዳችን ሕሊና ይማፀናሉ።**

**የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ሁኔታዎችን እየተከታተለ የሚደረጉትን የክህደት ድርጊቶች ማቅረቡን ይቀጥላል።**

**የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት በሃቀኛ ልጆቿ ይከበራል!!**

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!**

**የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**
**E-mail: ethiopianborder@yahoo.com**